
2017

# ፍሬያማ ሕይወት- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት




የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት ክፍል

9/24/2017

## ፍሬያማ ሕይወት

### መግቢያ

እግዚአብሔር በክርስትና ሕይወታችን ፍሬ እንድናፈራ ይፈልጋል። ይህንን ፍሬ የማፍራት ጉዳይ በቅዱስ ቃሉ በብሉይም በአዲስም ኪዳን ውስጥ ጎልቶ እናነባለን። ለምሳሌ የእግዚአብሔር ቃል እስራኤልን በተመለከተ እንዲህ ብሏል፡

> በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤
> በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ። (ኢሳ. 27፡6)

በዚህ ቃል መሰረት ያዕቆብ ያፈራ ዘንድ አስቀድም ስር መስደድ አለበት። ስር ከሰደደ ደግሞ ማበብና ቅርንጫፍ ማውጣት ይሆንለታል። ከዚያም ፍሬያማነት ይከተላል። ለሁሉም መሰረቱ ግን ስር መስደድ ነው። አንዱ ስር የምንሰድበት አቅጣጫ ቃሉን በማጥናት ነው። በቃሉ ስር ስንሰድ ቃሉ በሕይወታችን ይሰራል። በዚህ ጥናት የምናደርገውም ይህንኑ ነው።

በዮሐንስ 15፡ 1-11 ላይ እግዚአብሔር አብ ገበሬ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ የወይን ግንድ፣ ደቀመዛሙርት ደግሞ የወይኑ ቅርንጫር እንደሆኑ ያስተምረናል። የገበሬው ብዙ ድካምና ጥረት ከወይኑ ፍሬ ለማግኘት እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር አምላከም ከእኛ ከልጆቹ መንፈሳዊ ፍሬን ይጠብቅብናል። እግዚአብሔር አምላክ ካልዘራበት የሚያጭድ ጨካኝ አምላክ ስለሆነ ሳይሆን ክርስቶስ በኛ ውስጥ፤ እኛ ደግሞ በእርሱ ውስጥ ስላለን እንዲሁም የሚያስፈልገንን ሁሉ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ስለ ሰጠንና ዕለት ዕለትም እርሱ ስለተንከባከበንና ስለተጠነቀቀልን ነው። ከርሱ ዘንድ ያልተሰጠን ምንም ነገር የለም። ይህንን እውነት እንረዳ ዘንድ እግዚአብሔር አይኖቻችንን ያብራልን። የእኛ ድርሻ ግን ቅርንጫፍ መሆናችንን አምነን፤ ከጌታ ወደ እኛ በሚፈሰው ሕይወት ውስጥ መኖርና ፍሬን ማፍራት ነው። በዚህ መገለጥ ውስጥ ስንኖር ሕይወታችን የተትረፈረፈ ፍሬ ይኖረዋል።

እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቅብን ፍሬ፤ ደግሞም እርሱን የሚያከብረው የትኛው ነው? አፍርተን ከሆነ በብዙ እንድናፈራ የሚጠብቅብንስ? ፍሬያማ ሕይወት በተሰኘው በዚህ ጥናት ውስጥ መንፈሳዊ ፍሬዎችን እንማራለን። እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ፍሬዎች እንድናውቅ፣ እንድናፈራ አብዝተንም እንድናፈራ እግዚአብሔር አይኖቻችንን ይክፈት፤ በክርስቶስ ውስጥ በመኖር ይባርከን።

## ጥናቶች


| | |
|---|---|
| ጥናት አንድ | ፍሬን የማፍራት መሰረት |
| ጥናት ሁለት | የሚያፈራ ልብ |
| ጥናት ሶስት | በመንፈስ መመላለስ |
| ጥናት አራት | አዲሱን ሰው መልበስ |
| ጥናት አምስት | ሰማያዊ መሻት |
| ጥናት ስድስት | ራስን መግዛት |
| ጥናት ሰባት | ፍቅር |
| ጥናት ስምንት | መታዘዝ |
| ጥናት ዘጠኝ | ትህትና |
| ጥናት አስር | ትዕግስት |
| ጥናት አስራ አንድ | ይቅርታ |
| ጥናት አስራ ሁለት | ደስታ |
| ጥናት አስራ ሶስት | ሰላም |
| ጥናት አስራ አራት | አዕምሮን መጠበቅ |
| ጥናት አስራ አምስት | ቸርነት |
| ጥናት አስራ ስድስት | በጎነት |
| ጥናት አስራ ሰባት | የዋህነት |
| ጥናት አስራ ስምንት | አንደበት |
| ጥናት አስራ ዘጠኝ | እምነት |
| ጥናት ሃያ | አለመበቀል |

## ጥናት አንድ

## ፍሬን የማፍራት መሰረት

**ምንባብ፡-** ዮሐንስ 15፡ 1-11

**ዓላማ፡-** ፍሬን ለማፍራት በግንዱ በክርስቶ ላይ መጣበቅ እንዳለብንና ከእርሱ ውጭ ፍሬ ማፍራት እንደማንችል ለመማር።

**መግቢያ፡-** የክርስትና ግቡ ፍሬ ማፍራት ነው። የምናካሂዳቸው የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችና አገልግሎቶቻችን ሁሉ በሕይወታችን ክርስቶስን የሚመስል የሕይወት ፍሬ ካላፈራንባቸው አላማቸውን የሳቱ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ፍሬ ለማፍራት ማድረግ ያለብንን በቃሉ ያስተምረናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

(1) በክፍሉ ውስጥ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና አማኞች እንዴት ነው የተገለጹት?

(2) የወይን ግንድ በእስራዔል ታሪክ ምን ያመለክታል? ጌታ ኢየሱስ "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ" ያለውን ሃሳብ ከእስራዔል ማንነት አንጻር ተነጋገሩበት።

(3) ይህ ክፍል እግዚአብሔር አብን በገበሬ መስሎ ይገልጽልናል። አብ ገበሬ ነው የተባለው ለምን ይመስልሃል? ገበሬንና አብን ምን ያመሳስላቸዋል።

(4) ፍሬ የምናፈራበት መንገድ ምንድን ነው? ፍሬ ለማፍራት ምን እናድርግ?

(5) ፍሬ በማፍራታችን የሚከብረው ማን ነው?

(6) የምናፈራው ፍሬ ምንድን ነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

(1) በሕይወታችን የሚገለጡ እግዚአብሔር የሚከብርባቸው ፍሬዎች አሉ ወይ? ፍሬ እንዲበዛልን ምን እናድርግ?

(2) አማኞች "አምስተኛው ወንጌል ነን" የሚል አባባል አለ። ምን ማለት ይመስላችኋል።

## ጥናት ሁለት

## የሚያፈራ ልብ

**ምንባብ፦** ማቴ 13፡3-9፤ 18-23

**ዓላማ፦** በመንፈሳዊ ሕይወታችን ፍሬያማ ለመሆን ለእግዚአብሔር ቃል ያለን ምላሽ እጅግ ወሳኝ እንደሆነ ለማየት።

**መግቢያ፦** ኢየሱስ ለሕዝቡ በምሳሌ ያስተማረውን ትምህርትና ምሳሌው ምን ትርጉም እንዳለው ያብራራላቸውን ሃሳብ በዚህ ክፍል እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፦***

ማቴ. 13፡ 3-9 በመመልከት

1. ክፍሉ ምሳሌ አስተማራቸው ይላል። ምሳሌ ምንድን ነው?
2. በምሳሌው መሰረት ዘሪው የዘራባቸው የመሬት ዓይነቶች ስንት ናቸው?
   - ምን ዓይነት መሬቶች እናያለን?
   - መሬቶቹ ለዘሩ የሰጡት የፍሬ ምላሽስ እንዴት ነው ?
   - ይህንን የውጤት ልዩነት ያመጣው ምንድን ነው?

ማቴ. 13፡ 18-23 ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ምሳሌውን ሲያብራራላቸው እንመለከታለን።

3. ዘሩንና የተቀበለውን መሬት ኢየሱስ እንዴት ነው የተረጎመላቸው? (ከምን ጋር ነው ያያያዘው?)

4. ስንት ዓይነት ሰዎች እናያለን?

5. በዚህ ክፍል መሰረት ፍሬ የማያፈራ ልብ ምን ዓይነት ነው? ፍሬ የሚያፈራስ ልብ?
   - ለምንደን ነው የፍሬ ልዩነት (የውጤት ልዩነት) የመጣው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፦**

1. ለሕይወታችን የፍሬያማነት ልዩነት የሚያመጣው ምንድን ነው?
2. የእኛስ ልብ ከየትኛው ነው?

**ጥናት ሶስት**

**በመንፈስ መመላለስ**

**ምንባብ፡-** ገላ. 5፡ 16-26

**ዓላማ፡-** በምንፈስ ስንመላለስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በሕይወታችን እንደሚገለጡ ለመማር።

**መግቢያ፡-** ክርስቲያን በመንፈስ መመላለስ አለበት። ይህ ሲሆን ስጋዊነትን አሸንፈን በፍሬ የተሞላ የክርስትና ሕይወት ለመኖር እንችላለን። በዚህ ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬን በዝርዝር አናጠናም። በሌሎች ጥናቶች ስለ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ በዝርዝር እናጠናለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. ቁ. 16 መሰረት የስጋን ምኞት ላለመፈጸም ማድረግ ያለብን ምንድን ነው? በመንፈስ መመላለስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቁ 17-18 ያለውን ተመልክታችሁ የመንፈስን፣ የስጋንና የሕግን ግንኙነት ተናገሩበት።
3. ቁ. 19-21 ላይ የተዘረዘሩትን የስጋ ስራ የተባሉትን ተነጋግሩባቸው? ለምን የስጋ ስራ ተባሉ? የስጋን ስራ ማድረግ ውጤቱ ምንድን ነው?
4. ቁ. 22-23 ላይ የተዘረዘሩትን የመንፈስ ፍሬ የተባሉትን ተመልከቷቸው። በሚቀጥሉት ጥናቶች በዝርዝር ስለምታጠኗቸው በዛሬው ጥናት ለመግቢያ ያህል ብቻ በዳሰሳ ለማየት ሞክሩ። ለምን "የመንፈስ ፍሬ" የተባሉ ይመስላችኋል?
5. በቁ. 24 መሰረት ከክርስቶስ ጋር አብረን የሞቱ ተካፋዮች የመሆናችንን ፋይዳ ተነጋገሩ። በዚህ ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ ስጋ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህንን ሃሳብ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከሆነው ስጋችን ጋር እንዴት ታነጻጽሩታላችሁ?
6. ቁ. 25 እና 26 ተመልክታችሁ እንዴት በመንፈስ መመላለስ እንዳለብን ተነጋገሩ። በመንፈስ አለመመላለሳችን እንዴት ነው የሚገለጠው? ከዚህ አንጻር እርስ በርስ ያለን ግንኙነት እንዴት መሆን አለበት?

**ከሕይወት ማዘመድ፡-**

1. የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን የበለጠ እንዲገለጽ ከመንፈስ ቅዱስ ጋርና ከቃሉ ጋር ያለን ሕብረት እንዲያድግ ምን እናድርግ።
2. በሕይወታን የሚታይ ያልገራነው ቶሎ የሚገዳደረን የስጋ ስራ አለ ወይ? እንዴት ነው ይህንን አይነቱን ተግዳሮት አልፈን የድል ሕይወት ለመኖር የምንችለው?
3. ዛሬ ከዚህ ጥናት ምን ተማርን?

## ጥናት አራት

## አዲሱን ሰው መልበስ

**ምንባብ፡-** ኤፌ. 4፡17-32

**አላማ፡-** ክርስቲያኖች አሮጌውን ሰው አውልቀን እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን (የውስጥ) ሰው መልበስ እንዳለብን ለመማር።

**መግቢያ፡-** ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ዳግም ስንወለድ የውስጥ ሰውነታችን ሕያው ሆኗል። የውስጥ ሰውነታችን እግዚአብሔር ደስ ማሰኘት ይፈልጋል። ዳሩ ግን ከኛ ጋር የኖረ አዳማዊ ማንነታችን (አሮጌው ሰው) ደግሞ አብሮን አለ። አዲሱ ሰው እንዲጎለብትና ጎልቶ እንዲታይ አሮጌውን አዳማዊ ማንነታችንን አውልቀን መጣል አለብን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. ከቁ. 17-19 ያለውን ተመልከታችሁ አሕዛብ እንዴት እንደሚመላለሱ ተነጋገሩ። አሕዛብ እንዲህ እንዲመላለሱ ምክንያቱ ምንድን ነው? የአእምሮ ሁኔታ ለድርጊት ያለውን ተጽእኖ ተነጋገሩ።
2. ቁ. 20-21 ያለውን ተመልከታችሁ ክርስቶስ ለኛ የተገለጠው እንዴት እንደሆነ ተነጋገሩ? ስለ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጥልን ምንድን ነው?
3. ቁ. 22-23 አሮጌውን ሰው የምናስወግደው እንዴት ነው? አእምሮአችን የሚታደሰው እንዴት ነው?
4. ቁ. 24 የተጠቀሰው አዲሱ ሰው ማን ነው? ባሕሪውስ ምን ይመስላል?
5. ቁ. 25-29 እንዲሁም ቁ. 31 ተመልከታችሁ አዲሱን ሰው የምንለብስባቸውን ዝርዝርና ተግባራዊ መንገዶች ተነጋገሩ?
6. ቁ. 30 ተመልከታችሁ መንፈስ ቅዱስ ለምን እንደሚያዝን ተነጋገሩ?
7. በ. ቁ. 32 መሰረት ቅዱሳን እንዴት ነው መመላለስ ያለብን?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

1. አሮጌውም ሰው እንዲሁም አዲሱም ሰው ትግላቸው አእምሮችንን ለመግዛት ነው። አእምሮአችን (አስተሳሰባችን) በአዲሱ ሰው ተጽዕኖ ስር እንዲሆን ምን እናድርግ? አዲሱ ሰው እንዳይታይ የሚከለክል ማውለቅ ያለብን አሮጌ ነገር አለ ወይ?
2. መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ከኛ ጋር አብሮን አለ። እኛና መንፈስ ቅዱስ አብረን ስንኖር እያስደስትነው ነው ወይንስ እያሳዘንነው ነው?
3. ከዛሬው ጥናት ተነስተን ለመንፈሳዊ ፍሬያማነት የሚጠቅም ምን እርምጃ (የአቋም ለውጥ) ማድረግ አለብን?

## ጥናት አምስት

## ሰማያዊ መሻት

**ምንባብ፡-** ቆላ. 3፡1-11

**ዓላማ፡-** የጌታ ደቀ መዝሙር ለኃጢያት፣ ለስጋና ለምድራዊ ነገር የሞተ ስለሆነ፤ እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር ስለተነሳና ሕይወቱ በክርስቶስ ውስጥ ስለተሰወረ ለኃጢአት የሚያበረታቱትን ምድራዊ ብልቶቹን በመግደል መሻቱ በላይ ያለው እንዲሆን ለመማር።

**መግቢያ ፡-** በትንሳኤ ሕይወት የሚመላለስ ሰው ሕይወቱ ምን መሆን እንዳለበት ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆላስያስ ክርስቲያኖች የሰጠውን ምክር እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. ሐዋሪያው በላይ ያለውን አሹ/ፈልጉ የሚላቸው ለምንድን ነው?
2. ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. በላይ ያለውን እሹ ሲልስ ምን ማለቱ ነው?
4. በላይ ያለውን እየፈለጉ/እያሰቡ ደግሞም በምድር ያሉትን ብልቶቻችሁን ግደሉ ይላቸዋል፡፡
    - እነማን ናቸው?
    - አንዴት ነው የሚገድሉት?
    - ባይገደሉስ ምን ውጤት ያመጣሉ?
5. በተጨማሪም አስወግዱ የሚላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. አሮጌውን ሰው ከስራው ጋር ገፈው የጣሉት ለምንድን ነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

1. በእዚህ ክፍል እንደተማርነው እግዚአብሔር የእኛን ሕይወት ከክርስቶስ ጋር ሰውሮታል። እግዚአብሔር ይህንን ካደረገ የእኛስ ድርሻ ምንድን ነው?
2. የእያንዳንዳችን መሻትና ሃሳብ በላይ ያለውን ነው ወይንስ ምድራዊውን? ምንን ልንፈልግና ልንሻ ይገባናል?

## ጥናት ስድስት

## ራስን መግዛት

**ምንባብ፡-** 2 ጢሞ 1፡7፣ ምሳሌ 16፡32፤ ምሳሌ 25፡28

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር የሰጠን መንፈሰ እራስን የመግዛት መንፈስ እንደሆነና እራስን መግዛት አንዱ የመንፈስ ፍሬ እንደሆነ ለመማር፡፡

**መግቢያ፡-** በዛሬው ጥናታችን ሶሰት የመጽሐፍ ቅዱሰ ክፍሎችን በመመልከት ራስን መግዛት የሚባለውን የመንፈስ ፍሬ እናጠናለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

2 ጢሞ. 1፡7 በመመልከት

1. እግዚአብሔር የሰጠን መንፈሰ ምን አይነት መንፈስ ነው?
2. ይህ መንፈሰ በሁላችንም ውስጥ አለን?
3. ራስን መግዛት ምን ማለት ነው?
4. በዚህ ክፍል ራስን መግዛት ከሌሎች የመንፈስ ፍሬዎች ጋር መቀመጡ ምን ያመለክታል?

ምሳሌ 16፡32 በመመልከት

5. በዚህ ክፍል ውሰጥ የተነጻጸሩት ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. በትዕግስተኛነትና እራስን በመግዛት መካከል ምን ግንኙነት ታያለህ?
7. እራስን መግዛት ምን ያህል ዋጋ አለው?

ምሳሌ 25፡28 በመመልከት

8. ቅጥር ለከተማ ምንድን ነው? የፈረሰች ከተማስ ምን አይነት ናት?
9. መንፈስን መከልከል ማለት ምን ማለት ነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

1. እራስህን ለመግዛት የማያዳግት ፈታኝ ሁኔታ ውሰጥ ጎብተን እናውቃለን? እንዴት አለፍነው?
2. እራስን መግዛት ለለት ተለት ህይወት እንዴት ይጠቅማል? (ለምሳሌ በትዳር ውስጥ፤ ልጆችን በማሳደግ፤ በስራ ስፍራ ወ.ዘ.ተ.)
3. እራስን መግዛት በቤተ ክርስቲያን ካለን ዲሲፒሊን አንጻር እንዴት ይታያል (ለምሳሌ የፕሮግራም ሰአትን መጠበቅን በተመለከተ፣ የሚሰጠንን ሃላፊነት መወጣትን በተመለከተ ወ.ዘ.ተ.)

**ጥናት ሰባት**

**ፍቅር**

***ምንባብ፡-*** 1ቆሮ 13፡1-13

***ዓላማ፡-*** *ያለ ፍቅር የጸጋ ስጦታዎች፣ አገልግሎትም ሆነ መሰጠት ከንቱ እንደሆነ ለማየት።*

***መግቢያ፡-*** *በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችና አገልጋዮች ነበሩ። ነገር ግን ያላቸው ሁሉ ውጤታማ የሚሆነው ቁልፍ የሆነውን ነገር ሲከተሉ እንደሆነ ያስተምራቸዋል። የእኛም አገልግሎትና የጸጋ ስጦታዎቻችን ውጤታማ እንዲሆኑ ይህንን ቁልፍ ነገር መከተል ይኖርብናል። ይንን ዛሬ እንማራለን።*

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

ከቁ. 1-3

1. *ሐዋርያው እያነጻጸረ የሚናገራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? በዝርዝር ተመልከቱት። እያንዳንዳቸው ምን ማለት ናቸው?*
   - *እንዲህ አይነቱን አገልግሎት፣ መሰጠትና መስዋዕትነት የተሞላ አገልግሎት ከንቱ የሚያደርገው ምንድን ነው? ከንቱ ማለትስ ምን ማለት ነው?*
   - *ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመካከላቸው ስላለው መንፈሳዊ እንቅስቃሴና መስዋዕትነት የሞላበት አገልግሎትና ሕይወት እንዲገነዘቡ የፈለገው ምንድን ነው?*

ከቁ 4-7

2. *ፍቅርን እንዴት ነው የገለጸው?*
   - *ስለ ፍቅር የሚናገረው አሉታዊና አዎንታዊ ጉኑ ምንድን ነው?*
   - *በዚህ አገላለጽ ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው?*

ከቁ. 8-13

3. *ሐዋሪያው ምን ይናገራል?*
   - *ጸንቶ የሚኖረው ነገር ምንድን ነው?*
   - *ጸንቶ ከሚኖረው የሚበልጥ ምንድን ነው? ጸንቶ የሚኖር ሲል ምን ማለቱ ነው?*
   - *የሚሻርና ጸንቶ የሚኖረውን ነገር ለይቶ ማወቅ ለመልዕክቱ ተቀባዮች ምን ጥቅም ይኖረዋል?*

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-***

1. *አግልግሎታችን ከንቱ እንዳይሆን ዘወትር ልንከታተለው የሚገባን ነገር ምን መሆን አለበት?*
2. *ፍቅር ጸንቶ የሚኖር የማሻር ከሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ማወቅ በአገልግሎታችን ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምታችኋል? ምን ይጠቅማል?*
3. *ዛሬ ባጠቃላይ ከዚህ ጥናት ምን ተማርን?*

**ጥናት ስምንት**

***መታዘዝ***

**የምንባብ ክፍል፡-** 1ኛ ሳሙ 15፡ 1-23

**ዓላማ፡-** የተለያየ መስዋዕት ከማቅረብ ይልቅ እግዚሐብሔር የሚደሰትበትና የሚበልጠዉ ነገር እርሱን ማዳመጥና መታዘዝ እንደሆነ ለማየት።

***መግቢያ፡-*** በዛሬዉ ጥናታችን አግዚአብሔር ንጉስ እንዲሆን በህዝቡ በእስራኤል ላይ ወደ ቀባው ወደ ሳኦል በነብዩ በሳሙኤል በኩል የላከዉን ትዕዛዝ ተመልክተን እግዚአብሔርን መታዘዝ ያለውን ፋይዳ እናጠናለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. ከቁ. 1-3 ሳሙኤል ከአግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሳኦል ይዞ የመጣዉ ትዕዛዝ ምንድን ነዉ?
2. ከ. 4-9 ሳኦል ለመጣለት ትዕዛዝ ምን ምላሽ ሰጠ?

ከቁ. 10-16

3. ስለ ሳኦል ድርጊት ወደ ሳሙኤል የመጣዉ የአግዚአብሔር ቃል ምንድን ነው?
    - ለምንድን ነዉ አግዚአብሔር ትዕዛዜን አልፈጸመም አኔን ከመከተል ተመልሷል ያለው?
    - ለመጣለትስ የአግዚአብሔር ቃል የሳሙኤል ምላሽ ምን ነበር?
    - ሳሙኤል ለሳኦል ያለዉ፤ ሳኦልም የመለሰዉ መልስ ምንድን ነዉ?
4. ከቁ 17 ጀምሮ በመቀጠል የሳሙኤል መልስ ምን ነበር? የሳኦልስ?
    - ሳሙኤል በቁጥር 1 ላይና 17 ላይ በአግዚአብሔር ሰለ መቀባቱ፣ ከታናሽነት ወደ ንጉስነት መምጣቱን ማንሳቱ ሳኦል ምን እንዲገነዘብ ፈልጎ ነው?

ቁ. 9፤ 15፣ 20-21 ያለውን የሳኦልን መልስ ስንመለከት አርስ በእርሱ የማይስማማ ወይም የሚጋጭ ምን እናያለን? ለምን?

ከቁ 22-23

5. እግዚአብሔር የሚደሰተዉ በምንድን ነው?
    - ሰለ መታዘዝና ሰለ መስዋዕት በንፅፅር የቀረበዉ ምንድን ነው? ስለ መስዋዕት ምን ታውቃለህ?
6. የሳኦል ትልቁ ጥፋት ምንድን ነው? የአግዚአብሔርን ቃል መናቁ፣ አለመታዘዙ ምን ዉጤት አስከተለ?
7. በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት መታዘዝን በተመለከተ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን አስተዋልክ?

***ከሕይወት ጋራ ማዛመድ፡-***

1. ሰለ መታዘዝ ያለን መረዳት እስከዛሬ እንዴት ነበር?
2. በአለመታዘዝ ወይም ትዕዛዙን ማቃለል በሕይወታችን ምን ዉጤት ይኖረዋል?
3. በቀረው ዘመናችን እግዚአብኤርን በማዳመጥና በመታዘዝ ሕይወት ለመኖር ምን ወሰንን?

**ጥናት ዘጠኝ**

**ትህትና**

**ምንባብ፡-** ፊል. 2፡ 5-10

**ዓላማ፡-** በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ እርሱን የሚከተል ሁሉ ክርስቶስን ሊመስል ግድ ነዉና በክርስቶስ የነበረዉ የትህትና ሀሳብና ሕይወት የጌታም ደቀ መዝሙር ሊሆን እንደሚገባ ለማየት፡፡

**መግቢያ፡-** ሐዋርያው ጳውሎስ በፊሊጲስዩስ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ኢየሱስን እየገለጠላቸው እርሱን ምሰሉት ይላቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት በምን ሊመስሉት እንደሚገባ አናያለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. ሐዋርያው ምን እያለ ይመክራቸዋል?
2. ይህ በክርስቶስ ዉስጥ የነበረ ሃሳብ ምንድን ነው?
3. ሃሳቡን በዝርዝር ተመልከቱት ምን ማለት ነው?
    - በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር
    - መቀማት እንደሚገባ አልቆጠረዉም
    - በሰዉ ምሳሌ መገኘት
    - የባሪያን መልክ መያዝ
    - ባዶ መሆን
    - ለመስቀል ሞት መታዘዝ
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ባዋረደ መጠን እግዚአብሔር ምን አደረገው?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገዉን ስታይ ከእርሱ ምን ትማራለህ?
6. ከዚህ ሃሳብ በመነሳት በሕይወትህ ዉሰጥ ያንተ ድርሻ ምንድን ነው? የአግዚአብሔርስ?

**ከሕይወት ጋራ ማዛመድ፡-**

1. በሕይወታችን ለእግዚአብሔር ክብር ለሌሎች ጥቅም ወደንና ፈቅደን የተዉነው የሚገባን ስፍራ አለ?
2. ከሌለ ይህ የክርስቶስ ሀሳብ በአንኛ ዉሰጥ አንዲሆን ልናደርገዉ የሚገባን ነገር ምን አንደሆነ አስተዋልን? ምን ተማርን?

## ጥናት አስር

## ትዕግስት

**ምንባብ፡-** 1 ጴጥ. 2፡ 1-25

**ዓላማ፡-** ክርስቲያን አንዱ የተጠራበት ምክንያት መልካምን እያደረገ በግፍ ስለሚደርስበት መከራ እየታገሰ እንዲኖርና ይህም ከእግዚአብሐር ዘንድ ምስጋና እንደሚሆንለት ለማሳየት፡፡

**መግቢያ፡-** እግዚአብሔር በእማኝ ሕይወት ዉስጥ እንዲኖሩ ከምፈልጋቸው ፍሬዎች መካከል አንዱ ትዕግስት ነው። ዛሬ ይህንን የመንፈስ ፍሬ እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ጸሐፊዉ በስደት ለተበተኑት ቅዱሳን በፍርሃት እንዲገዙ የሚነግራቸው ለነማን ነው?
2. ሰዉ መከራን የሚቀበለዉ በስንት መንገድ ነው? በምንና በምን?
3. አማኝ ሊቀበለዉ የሚገባው መከራ የትኛዉ ነዉ? በቁጥር 19 መሰረት መከራዉንስ እንዴት ሊቀበለዉ ይገባል?
4. መልካምን አድርጎ በግፍ መከራን የመቀበልስ ዉጤት ምንድን ነው?
5. ክርስቲያን መልካምን እያደረገ ለምን መከራን እንዲቀበል ተደረገ?
6. ጌታ በግፍ መከራን ሲቀበል የታገሰበትን መንገድ በዝርዝር ተመልከቱት።
7. በቁጥር 21 መሰረት ክርስቶስ ይህንን ያደረገዉ ለምንድን ነው?
8. በመከራ ዉስጥ የሚያልፉት ቅዱሳን ይህንን መልዕክት ሲሰሙ ምን እንዳያስተውሉ የሚረዳቸዉ ይመስልሀል?

### ከሕይወት ጋራ ማዛመድ፡-

1. በምን መንገድ መከራን እየተቀበልን ነዉ?
2. እየተቀበልነው ያለውን መከራ እንዴት እያየነውና እየተቀበልነው እንገኛለን? ወደፊትስ እንዴት ሊሆን እንደሚገባዉ ከጥናቱ ምን ተማርን?
3. በግፍ የሚደርስብን መከራ መታገስ ምን ትርፍ አለው?

## ጥናት አስራ አንድ

## ይቅርታ

**ምንባብ፡-** ማቴ 18: 21-35

**ዓላማ፡-** ደቀ መዝሙር በሕይወቱ ሊታይ የሚገባው አንዱ ፍሬ የይቅርታ ሕይወት ነው። ይቅርታችን ያለ ገደብ እንዲሆንና ይቅርታ ማድረግ ለራስ ጥቅም እንደሆነ እንድናስተውል።

**መግቢያ፡-** ጴጥሮስ ስለ ይቅርታ ራሱ የተረዳበትና መልካም የመሰለው መንገድ አለ፡፡ ይህንን አስተሳሰቡን በጌታ ፊት ትክክል እንደሆነ በጥያቄ ያቀርባል፡፡ በዚህ ክፍል የይቅርታን ሕይወት ከጌታ እንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. ጴጥሮስ ምን ሲል ነው ጌታን የጠየቀው? ለምን?
2. ጌታስ ምንን መልስ ሰጠው?
3. ስለ ይቅርታ ጌታ የሰጠውን ምሳሌ በዝርዝር ተመልከቱት።
4. ከምሳሌው ምን እንማራለን?
5. ይቅርታን ያለማድረግ የሚያስከትለው ጉዳት ምን እንደሆነ አስተዋልክ?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-

1. ይቅርታን ያላደረግንለት፣ በደሉን ያልተውንለት ሰው አለ?
2. ወደ ፊት የሚበድሉንን ሁሉ ይቅር የምንለው ለምን እንደሆነ ተረዳን?

## ጥናት አስራ ሁለት

## ደስታ

**ምንባብ፡-** ዕንባቆም 3፡ 17-19

**ዓላማ፡-** በምናልፍበትና ባለው ሁኔታ ውስጥ ጌታ ዝም ያለ ቢመስል አንኳን በእርሱ ደስ መሰኘት እንዳለብን ለማሳየት፡፡ ነገሮች ባይሟሉም፣ ባይሳኩም በጌታ ደስ መሰኘት ከአማኝ እንደሚጠበቅ ለማሳየት።

**መግቢያ፡-** በዛሬው ጥናታችን እግዚአብሐር ደስታን በሕይወታችን ሊያይ እንደሚወድና ምን አይነት ደስታ በሕይወታችን ሊያይ እንደሚወድ አንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. በዚህ ክፍል ላይ ዕንባቆም ምን ምን ሲል እናያለን?
2. አነዚህ ባይኖሩም ብሎ የሚላቸው ነገሮች ምን ያህል አሰፈላጊ ናቸው?
3. የዕንባቆም የሕይወቱ ውሳኔ ክብደት ምን ያህል ነው?
4. ከውሳኔውና ከዚያም በመቀጠል ሰለ እግዚአብሐር ለሚገልጸው ነገር ዕንባቆም እግዚአብሔርን አንዴት ነው የተረዳው?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-

1. ዛሬ ባለብን የሕይወት ጥያቄና ችግር አንዲሁም ካልሞላልን ነገር ባሻገር ምን ያህል ደስተኞች ነን?
2. ዕንባቆም የሚለው ዛሬ በሕይወታችን ቢያልፍ እውነተኛ ደስታ በጌታ ይኖረናል?
3. እሰከ አሁን በምን አይነት ጉድለት አልፈናል? ያንን ግዜ እንዴት አለፍነው? ወደፊትስ ተመሳሳይ ሁኔታ ቢያጋጥመን እንዴት እናልፈዋለን? ከጥናቱ ምን ተማርን?

**ጥናት አስራ ሶስት**

**ሰላም**

**የንባብ ክፍል፦** ኢሳ. 9፡6፤ ፊል. 4፡7፣ ዮሐ. 14፡27

**ዓላማ፦** በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነውን ሰላም ለማወቅና በዚህ ሰላም ውስጥ እንድኖር ለማበረታታት።

**መግቢያ፦** ሰው ሁሉ ሰላምን ይፈልጋል። ሰላምን ለማግኘት ሰው ብዙ ነገሮችን ያደርጋል። ነገር ግን አለማችን በነውጥና በሁካታ የተሞላች ነች። እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ግን የሰላም አለቃ የሆነውን ክርስቶስን በማወቅና በመቀበል ነው። በዚህ ጥናት በክርስቶስ የተቀበልነውን ሰላም እንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፦***

1. ኢሳ. 9፡6 ላይ ጌታ ኢየሱስ "የሰላም አለቃ" የተባለው ለምንድ ነው?

ዮሐ. 14፡27ን በመመልከት

2. ጌታ በሚሰጠው ሰላም እና አለም በሚሰጠው ሰላም መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

3. ጌታ ልባችሁ አይታወክ፤ አይፍራም ያለውን እርሱ ከሚሰጠው ሰላም አንጻር ተነጋግሩበት።

ፊል. 4፡ 7ን በመመልከት

4. የእግዚአብሔር ሰላም ባህርይ ምንድን ነው? "አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ ሰላም" ምን ማለት ነው?

5. የእግዚአብሔር ሰላም በሕይወታችን ምን ይሰራል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

1. ረብሻ፣ ሑከትና የማይመች ሁኔታ ውስጥ እያለፍን ሰላም ኖሮን ያውቃል ወይ? እንዲህ ያለ ልምምድ ካለን ምክንያቱ ምን ይመስላችሁኋል? ተነጋገሩበት።

2. ሰላም በአውሎ ንፋስ መካከል በእርጋታ መቀመጥ ነው ይባላል። ትስማማላችሁ ወይ? ይህ በተጨባጭ እንዴት እንደሚቻል ተነጋግሩ።

3. በሕወታችን ሰላም ስናጣ ምን እናድርግ?

## ጥናት አስራ አራት

## አይምሮን መጠበቅ

**የምንባብ ክፍል፦** ፊል. 4፡ 4-9

**ዓላማ፦** አዕምሮንና ልብን በጸሎትና ክቡር በሆኑ ነገሮች በመሙላት ከጭንቀት ማረፍ እንደምንችል ለመገንዘብ፡፡

**መግቢያ፦** በዛሬዉ ጥናታችን ደስታ በማን እንደሆነና ከጭንቀት እንዴት እንደምናርፍ እናጠናለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፦***

1. ጳዉሎስ በመደጋገም ደስ ይበላችሁ ይለናል (4፡4)። "በጌታ ደስ ይበላችሁ" ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጳዉሎስ የሚናገረዉ ደስታ በሁኔታዎች ሁሉ ዉስጥ ነው። እንዴት በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ደስታ ይገኛል?
3. በጭንቀት ጊዜ ፀሎት የመጀመሪያ የመከላከያ መሳሪያ የሚሆነው ለምንድን ነዉ (4፣6)?
4. በፀሎታችን መሀል ለምንድነዉ አመስጋኞች መሆን ያለብን?
5. በጭንቀት የሚባዝን አይምሮአችንን በምን እንድንሞላው ነው በቁጥር 8 ላይ የታዘዝነዉ? ይህስ ከጭንቀት እንዴት ያሳርፈናል? (አስቡ የሚላቸዉን ነጥቦች ከጭንቀት ጋር አነጻጽሯቸው።)
6. መልካም የሆነ ሃሳብን በማስብ ጭንቀትን ወይም ፍርሃትን ለማሸነፍ የምንችልበትን ምሳሌ ተነጋገሩ።

**ከሕይወት ጋራ ማዛመድ፦**

1. ብዙ ጊዜ እንድንፈራና እንድንጨነቅ ከሚያደርጉን ነገሮች ዉስጥ አንዳንዱን በመጥቀስ ተነገገሩ? ለምን እንደዚህ የሚሰማን ይመስላችሁኋል?
2. ጳውሎስ "ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበለላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ" ይላል። እንደ ሞዴል የምንከተለው ሰው አለን ወይ?
3. ጌታ ለያንዳንዳችን (ላንተ/ላንቺ) ቅርብ ነው ወይ?

## ጥናት አስራ አምስት

## ቸርነት

**ምንባብ፦** 2ቆሮ 8፡1-15

**አላማ፦** የጌታ ደቀ መዝሙር ከጌታ ያየውንና የተቀበለውን ቸርነት ሊያደርግና ሊለማመድ እንደሚገባ እንዲሁም ቸርነት ለማድረግ የግድ ባለ ጠጋ መሆን እንደማያስፈልግ ለማሳየት።

**መግቢያ፦** ጳውሎስ የቆሮንጦስ ክርስቲያኖችን ስለ ልግስና የሚያበረታታበትን ምክር ዛሬ ለራሳችን እንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፦***

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መቄዶንያ አብያተ ክርሰቲያን ምን እያለ ይናገራል?
2. እንደዚህ የሆኑበት ምክኒያት ምንድን ነው ይላቸዋል?
3. ለቆሮንጦሰ አማኞች ምን አድርጉ እያለ ያበረታታቸዋል? ለምን?
4. በበጎ ፈቃዳቸው በሚያደርጉት ቸርነት ምን ላይ መጠንቀቅ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፦**

1. የመቄዶንያ ክርስቲያኖች ቸርነትና እያንዳንዳችን ስለምናደርገው ቸርነት ሰናነጻጽር ምን ይሰማናል?
2. ቸርነትን የማድረጋችን ምክንያት ምንድን ነው?
3. ቸርነት ልናደርግለት የሚገባን ሰው በቅርብም ይሁን በሩቅ ፈልገን ካለን ላይ በዚህ ሳምንት ውስጥ እናካፍል።

## ጥናት አስራ ስድስት

## በጎነት

**የንባብ ክፍል፡-** “እግዚአብሔርን። አንተ ጌታዬ ነህ አልሁ፤ ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም።" (መዝሙረ ዳዊት 16:2)

"እርሱም። ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው።" (የማቴዎስ ወንጌል 19:17)

**ዓላማ፡-**

1. በጎነት በዙርያችን ያሉትን ሰዎች የምናመልከው አምላክ ማን እንደሆነና ምን እንደሚመስል የምናሳይበት አንዱ መንገድ እንደሆነ ለመማር።

2. ከእግዝአብሔር የመለኮቱ ባህሪ ተካፋይ እንደሆንን በማወቅ በበጎ ስራ ሁሉ እንድንበዛ ለመነሳሳት።

***መግቢያ፡-*** በዛሬው ጥናት በጎነት ከእግዝአብሔር የወረስነው ባህሪ እንደሆነ ከቃሉ እንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. በጎነት ማለት ምን ማለት ነው?

2. በበጎነትና በቸርነት መካከል ምን ዝምድናና ልዩነት አለ?

3. ሰው ያለ እግዝአብሔር በጎነት ይገኝበታልን?

4. በጎነት ክርስትያናዊ ባህርያችን መሆን ለምን አስፈለገ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

1. በጎነትን በማድረጋቹህ ምክንያት ሰዎች እንዴት እግዝአብሔርንና እናንተን እንድያመሰግኑ ምክንያት እንደሆነ ልምምዳችሁን አካፍሉን።

2. በጎነትን በማድረጋችሁ የተሰማችሁን ውስጣዊ ስሜት አካፍሉን።

## ጥናት አስራ ሰባት

## የዋህነት

**የንባብ ክፍል፡-** ማቴ 11፡29 ፤ ሰፎ.3፡12 ፤ ያዕ 3፡13 ፤ 1ኛጴጥ 3፡13

**ዓላማ፡-** የዋህነት ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል አንዱ እንደሆነና ጌታም እንድንማረው የሚገባ መሆኑን እንደሚፈልግ ለመረዳት።

**መግቢያ፡-** ዛሬ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ስለሆነው ስለ የዋህነት እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. በማቴ 11፡29 መሠረት ኢየሱስ ከእርሱ እንድንማር የሚነግረን ምንድም ነው?
2. የዋህ ማለት ምን ማለት ነው?
   በሰፎ 3፡12 መሠረትስ?
3. ከእርሱም ባህሪና ማንነት የዋህነትን መማርና እርሱንም በዚህ ባህሪ መምሰል ውጤቱ ምንድን ነው?
4. በያዕ. 3፡13 እና 1ኛጴጥ 3፡13 መሠረት
   - በሕይወታችንና በግንኙነታችን ውስጥ የዋህነት እንዴት ሊገለጥ ይገባዋል?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-

1. የእግዚአብሔር ቃል እንደ እርግብ የዋህዎች፣ እንደ እባብ ልባሞች እንድንሆን ይመክረናል። መቼ ነው የዋህ መሆን ያለብን? መቼስ ነው ልባም መሆን ያለብን?
2. የዋህ በመሆናችን እንደ ሞኝ የተቆጠርንበት ሁኔታ አለ? እንዴት አለፍነው?

**ጥናት አስራ ስምንት**

**አንደበት**

**ምንባብ፡-** *ያዕ* 3: 1-12፤ *ማቴ* 12፡ 33-37

**ዓላማ፡-** ከአንደበታችን የሚወጣው ሁሉ በልባችን የሞላው እንደሆነ በማወቅ የጌታ ደቀ መዝሙር የሆነ ሁሉ ለአንደበቱ እጅግ ሊጠነቀቅ እንደሚገባው እንድናስተውል።

**መግቢያ፡-** አንደበታችን ለመልካምም ለክፉም ሊውል እንደሚችል በማሳሰብ፤ አንደበታችችንን የምንገዛበትን መንገድ እንማራለን፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. ያዕቆብ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ እያለ ለምን ይመክራቸዋል?
2. አንደበትን (ምላስን) በምን በምን ይመስላቸዋል?
3. አንደበት በእሳት የተመሰለው ለምንድን ነው?
4. የአንደበትን አጠቃቀም በተመለከተ ያዕቆብ ያለውን ተነጋገሩ፡፡
5. ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 12፡ 33-37 ላይ ስለ አንደበት የገለጸው ምንድን ነው?
6. አንደበትን ለመግዛትና መልካም ለማድረግ ምን ያስፈልጋል?
7. አንደበትን አለመግዛትና አለመጠንቀቅ ምን ውጤት አለው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

1. በአንደበታችን የሳትንበትን ጊዜ እናስብ፡፡ ወደፊትስ እንዳንስት ዛሬ ከተማርነው ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ምን ልናደርግ ይገባናል?

2. በአንደበታችን መልካም ያደረግንበትን ጊዜ እናስብ፡፡ ይህ አይነቱ ነገር እንዲበዛልን ምን ማድረግ አለብን?

## ጥናት አስራ ዘጠኝ

## እምነት

**ምንባብ፡-** ዕብ 11፡ 1-12

**ዓላማ፡-** ክርስቲያን በሕይወቱ የሚያደርጋቸውና ኑሮው በእምነት መሆን እንዳለበት፣ በእምነት መኖር እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኘውና ዋጋም እንዳለው ለማየት።

**መግቢያ፡-** በዚህ ክፍል ስለ እምነት ትርጉምና የእምነት ሰዎች አቤል፣ ሄኖክ፣ ኖህ፣ አብረሃምና ሳራ እግዚአብሔርን በእምነት እንዴት ደስ እንዳሰኙ እንማራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. እምነት ምንድን ነው?
2. የሚታዩት ነገሮች እንዴት መጡ? ከእምነት ጋርስ እንዴት ይያያዛል?
3. ለሽማግሌዎች የተመሰከረው በምንድን ነው?
4. እግዚአብሔር ለምን የአቤልን መስዋዕት ተቀበለ?
5. ሄኖክን እግዚአብሔር ለምን ወሰደው?
6. ኖህ በእምነት መርከብን ሰራ ማለት ምን ማለት ነው?
7. ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ ምን ያስፈልገዋል?
8. እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኘው በምናችን ነው? እንዴት?
9. ከአብረሃምና ከሳራ ህይወት ስለ እምነት ምን እንማራለን?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

1. ኑሮአችን በእምነት ነው? አገልግሎታችን በእምነት ነው? ጌታን መጠበቃችንስ በእምነት ነው?
2. ስለ እምነት ልምምዳችን ለቡድናችን እናካፍል።

## ጥናት ሃያ

## አለመበቀል

**የምንባብ ክፍል፡-** ሮሜ 12፡ 17-21

***መግቢያ፡-*** በዛሬዉ ጥናት በቀልን ለጌታ ስለመተው እና ከሰዉ ሁሉ ጋራ በሰላም ስለመሆን የተሰጠዉን ወርቃማ ምክር እንመለከታለን፡፡

**ዓላማ፡-** ክፉትን በመልካም መመለስና በቀልን ደግሞ ቅን ፈራጅ ለሆነ ጌታ መተዉ የአማኝ ባህሪና በሰላም የመኖር መርህ እንደሆነ ለመረዳት።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. አንድ ሰዉ በንብረትህ ላይ ጉዳት አድርሶ ቢሄድ ምላሽህ ምንድን ነው? ለምን?
2. ብዙ ጊዜ ለምንድን ነዉ ክፉን በክፉ ለመመለስ የምንፈተነው?
3. አንዳንድ ሰዎች ክፉን በክፉ የሚመልሱበትን ምሳሌ ግለጽ?
4. በቁጥር 19 የተዘረዘሩትን ሶስት ነጥቦችን ግለጽ። የቁጥሩ ቁልፍ ሀሳብ ምንድን ነው?
5. በቀል ብዙ ጊዜ ዉጤቱ አስከፊና አደገኛ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?
6. ጳዉሎስ ከሌሎች ጋራ ቢቻላችሁ በሰላም ኑሩ ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?
7. አግዚአብሔር በቀል የርሱ ብቻ እንደሆነ የሚያስጠነቅቀን ለምንድን ነው?
8. የእግዚአብሔር በቀልና የእኛ በቀል የሚያመጣዉ ዉጤት ምን እንደሆነ ግለጽ?
9. በቁጥር 20 ላይ ጳዉሎስ ከምሳሌ 25፡ 21-22 ጠቅሷል። ከመበቀል ይልቅ ምን ማድረግ ነዉ ያለብን?
10. “በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና” ሲል ምን ማለቱ ነው?

**ከሕይወት ጋራ ማዛመድ፡-**

1. ይጠላናል ብለን ለምንገምተው ስው ከውሃና ከምግብ ሌላ ልንሰጠዉ የምንችለዉ ነገር ምን አለ?

2. በቅርብ ጊዜ ዉሰጥ ወይም የቆየ አንድ ያሳዘነን ሰዉ ካለ አናስብ። ከዚያ ሰዉ ጋራ ሰላም ለመፍጠር ልናደርገው የምትችለዉ መልካም ነገር ምን አለ?

3. በዉስጣችን ያለዉን የእግዚአብሔርን ሰላም ለመጠበቅ እንዴት እንደምትችል ይሄ ክፍል ምን ያስተምረናል?